- አትመው የሚያውቁ ከሆነ ካለው/ችው ተማሪ ጋር እንዲወያዩ እና ለክፍል እንዲገልጹ አድርግ፡፡ የተማሪዎችን ገለጻ ካዳመጥክ/ሽ በኋላ አመስግነህ/ሽ ስለ ህትመት ፍቺ /ትርጉም/ ግለጽ፡፡ ህትመት ማለት አንድ ዲዛይን/ቅርጽ በማዘጋጀት ወይም አንድ በተፈጥሮ ያለን ነገር ቀለም በመቀባት፣ቀለም በመንፋት ወስጥ በመንከር እና እውስጥ በመቀባት እንዲሁም ሌሎች ዘዴዎችን/ስልቶችን በመጠቀም ዲዛይኑን /ቅርጹን/ እየደጋገሙ እንዲያባዙ /እንዲያትሙ/ በደንብ አብራራ፡፡

ልምምድ አንድ (1)

- ለብሎክ ህትመት እራ ስልት/ዘዴ/ አስፈላጊ ነገሮች
- ዲዛይኑን እላዩ ላይ የምንሰረባቸው እንደ እነ-ጣውላ፣ድንች፣ቀይ ስር፣ፕላስቲክ እና የመሳሰሉት፡፡
- ቅርጽ/ዲዛይን/ የሚወጣባቸው ስለት ያላቸው ነገሮች እንደ መቀስ፣ቢላዋ እና የመሳሰሉት፡፡
- ዲዛይኑ እላዩ ላይ የሚታተምበት እንደ ወረቀት.፣ልብስ የመሳሰሉት
- የተለያዩ መልክ ያላቸው ቀለሞች መቀባት፡፡

  የብሎክ ህትመት ስራ ስልት /ዘዴ/
- ዲዘይኑ እላዩ ላይ የሚሰራበትን ነገር ማዘጋጀት፡፡
- የተፈለገውን ዲዛይ ሊሰራበት በታቀደው ነገር ላይ መንደፍ፡፡
- የተሰራውን ዲዛይን መስመር በመከተል ስለት ባለው ነገር /መቃስ/ መቁረጥ የዲዛይኑን ዙሪያ ወይም ከውስጥ መውጣት ያለበትን ጥርግ አድርጎ ወደታች በማጎድጎድ እንዲያወጡት ማስገንዘብ፡፡
- የተዘጋጀወን ዲዛይን ቀለም መቀባት፡፡
- ቅርጽ የወጣለትን ዲዛይን በተፈላጊው ነገር ላይ ማተም አለባቸው፡፡

- የዚህ ቅርፅ ስራ የፊደላት ህትመት ሲሆን፡- ከቀኝ ወደ ግራ በመገልበጥ ቅርጹ ሊሰራ በተዘጋጀው ነገር ላይ መስራት አስፈላጊ እና ግዴታ መሆኑን አስገንዝግ/ቢ፡፡ ምክንያቱም የተሰራው ቅርጽ ሲታተም ወደ ቀኝ ዞሮ መታተም እንዳለበት ማወቅ አለባቸው፡፡
- የብሎክ ህትመት ስልት/ዘዴ/ ከብዙ ነገሮች መዘጋጀት ቢችልም ለመስራት ቀላል የሆኑ ነገሮች እንደ ድንች፣ጣውላ፣ ጎማ /ፕላስቲክ/ ፣ቀይስር ፣ካሮት እና ከመሳሰሉት ላይ መሰራት እንደሚችል በደንብ ግለጽላቸው፡፡

## ከድንች መስራት

- ለዚህ ስራ ምቹ የኖነ ድንች ይምረጡ
- የተመረጠውን ድንች እኩል ሁለት ቦታ ይቁረጡት
- የተፈለገውን ዲዛይን በሁለት በተከፈለው ድንች ፊት /በተቆረጠው በኩል መስራት አለባችሁ፡፡
- የሰራኸውን ዲዛይን በመተው ዙሪያውን በስለት በመጠቀም ወደ ውስጥ በማጎድጎድ ወይም በሌላ መልክ ዲዛይኑን ከውስጥ ወደ ታች በማጎድጎድ እንዲሰሩ ማስገንዘብ፡፡
- ከዚህ በላይ ተሰርቶ የተዘጋጀውን ዲዛይን ቀለም በመንከር /በመቀባት/ ሊሰራበት ከተዘጋጀው ነገር ላይ ወደታች ተጭኖው ማተም እንዳለባቸው እና እንደገና እያነሱ በሌላ ነገር ላይ ደጋግመው እንዲያትሙ ግለጽላቸው፡፡
- በዚህ ስልት ወይም ዘዴ መስራት ስትጀምር ቀላል ጂኦ ሜትራዊ ዲዛይን ካላቸው ነገሮች ላይ በመነሳት አስፈላጊ መሆኑን ማስገንዘብ፡፡

## በዚህ ስራ ውስጥ መጠናቀቅ የሚገቡ ነገሮች

- የዚህን ዲዛይን ቅርፅ ከውስጥ ለማውጣት እና ለመቁረጥ የምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች ስለታም ስለሆኑ እንዳይቆርጣቸው መጠንቀቅ እንዳለባቸው ማስገንዘብ ፡፡
- ዲዛይኑ ወደ ውስጥ ሊጎደጉድ የሚገባው 3-4 ሚሊ ሜትር መብለጥ እንደሌለበት ማሳወቅ፡፡
- ዲዛይኑ በሚሰራበት ወቅት ወይም ግዜ እንዳይሰበር፣እንዳይሸረፍ እና እንዳይሰነጠቅ መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ማስገንዘብ፡፡

ከዚህ በላይ የተሰጠውን የብሎክ ህትመት ስራ ሂደት ስልት ለተማሪዎች ካስገነዘብህ በኋላ ድንች ካገኘህ በድንች ፤ድንች ካጣህ የሚተካውን ነገሮች እንደ ቀይስር፣ካሮት፣ስኳር ድንች እና የመሳሰሉትን በመጠቀም ፊደል ወይም ቁጥር ቀ ላይ ቅርጽ ያለው ዲዛይን ሰርተህ/ሽ ለተማሪዎችህ/ሽ አሳይ፡፡ እርስ በራሳቸውም እንዲሰሩ በክፍል አበረታታቸው፡፡

2.የብሎክ ህትመት በድንች ክፍል ውስጥ ተለማምደው በኋላ ከጫማ ሶል ስማቸውን እላዩ ላይ ጽፊው እንደ ማህተብ እቤታቸው ሰርተው እንዲመጡ አበራታቷቸው፡፡

ማሳሰቢያ፡ የማህተም ስራውን በምስማቸው ሲሰሩ ፊደሎቹን ገልጠው እንዲቀርጹ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ኦደ የሚል ማህተም ለመስራት ብንፈልግ እንደ አንደኛው ላይ ላዩን ገልበጠን እንጽፋለን ማለት ነው፡፡

1. **ዳኦ ፡ ይህ በሚገለበጥበት ግዜ** 2. **ኦዳን ይሰጣል፡፡**

## 2.2.2. የኮላጅ እና የሞዛይክ ስራ

### 1.ኮላጅ

**ተግበር 4**

መምህር/ት ይህ ይዘት ቀድመህ የተለያዩ ነገሮችን ለመጠቀም በቀላሉ ተዘጋጅተህ ተማሪዎችን የኮላጅን ትርጉም ፍቺ እንዲገነዘቡ አብራራላቸው፡፡ ለጥያቄ አራት መልስ ከዚህ በታች ባለው አብራራ፡፡ ኮላጅ ከፈረንሳይ አባባል የመጣ ሲሆን የተቆራረጠ ወረቀትን በአንድ ነገር ላይ የማጣበቅ (የማስያዝ) ዘዴ መላት ነው፡፡ ኮላጅ አርት ከሚሰራባቸው ስራዎች አንዱ ሆኖ በታዋቂ አርቲስቶች ከ1ኛው ምእተ አመት በፊት የተጀመረ ስራ ነው፡፡ አርቲስቶች በዚያን ግዜ የኮላጅ ስራን የጀመሩት የተለያዩ የቀለም ቅብ ስራ ወይም የመጽሀፍ ጽሁፍ ስራን በማቀናጀት መስራት ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም የኮላጅን ትርጉም መረዳት አለመረዳታቸውን ለማወቅ የኮላጅን ትርጉም እና ምንነት ጠይቃቸው፡፡



በአበባ መልክ በምስር ፍሬ የተሰራ ምስል የሚያሳይ ነው፡፡ ብርቱካናማ መልክ ያለው በአበባው ላይ የሚታየው የተለጠፈው የተከካ የምስር ፍሬ ሲሆን መሃል እንብርት ላይ

የሚታየው ደግሞ እንደ ጥቁር ቀለም የሚመስለው ያልተከካ ድፍን ምስር የተሰራ ነው፡፡ ውብ እና የሚያማምሩ ስራዎች በዚህ መልክ መስራት ይቻላል፡፡

ልምምድ 2

**ሀ. ለኮላጅ ስራ የሚያስፈልጉ ነገሮች**

**I.የሚጣበቁ ነገሮች**

እንደ ወረቀት፣መጽሄት፣ፎቶዎች፣አፈር፣ልብስ ፣ጸጉር፣ሰር፣ቅጠል፣የአእዋፍ ላባ፣የእህል ፍሬ እና የጽዋትና የመሳሰሉትን እንደ አስገላጊነታቸው ቀድሞ ማዘጋጀት እንዳለባቸው መንገር እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ ከሆኑ ቀለም በመቀባት ከተሰራው ነገር ጋር እንዲመሳል ማድረግ ይቻላል፡፡

**II. የሚያጣብቁ ነገሮች**

ለማያያዝ የሚያገለግሉ እንደ ኮላ፣ኡሁ፣ሙጫ፣ቁልቋል እና የመሳሰሉትን መጠቀም ይቻላል፡፡

**III. የሚጣበቁበት ነገሮች**

ወፍራም የሆኑ ነገሮች እንደ ወረቀት፣ካርቶን፣ ኮምፖርሳቶ፣ጠፍጣፋ እንጨት እና የመሳሰሉትን በማጣበቅ መስራት፡፡

**ለ. የኮላጅ ስራ አሰራር ዘዴ**

- የኮላጅን ስራ ለመስራት በቅድሚያ የሚሰራው የስዕል ዲዛይን በሚሰራው ነገር ላይ እንደ ጠፍጣፋ እንጨት፣ወፍራም ወረቀት እና የመሳሰሉት ላይ ቅድሚያ መነደፍ እንዳለበት አስገንዝባቸው፡፡
- የምናጣብቅባቸውንም ነገሮች ማዘጋጀት አለብን፡፡
- የተሰራው ንድፍ ላይ አስፈላጊ በሆነ ቦታ በጥንቃቄ ኮላ ወይም ማጣበቂያ መቀባት፡፡
- ለመጣበቅ የተዘጋጀው እንደ ወረቀት፣ጸጉር፣የዶሮ ላባ እና የመሳሰሉትን አስፈላጊ በሆነው ቦታ እንደሚሰራው ስራ መልክ እላዩ ላይ ማጣበቅ እንዳለባቸው አስመዝግብ፡፡
- በጥሩ ሁኔታ ያጣበቅናቸውን እስኪደርቁ ድረስ ከቦታው ሳናቀሳቅስ ማቆየት አለብን፡፡

የኮላጅ ስራን አሰራር ዘዴን ከዚህ በላይ ተዘርዝሮ እንዳየኸው ለተማሪዎች ካስገነዘብክ በኋላ ያለውን ቅደም ተከተል በመከተል ተማሪዎች ቀለል ያሉ ስዕሎችን በአካቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ላይ የኮላጅን ስራ እንዲሰሩ አበረታታቸው፡፡

## 2.ሞዛይክ

## ውይይት 2

መምህር/ት በዚህ ይዘት ላይ አስቀድመው ከተዘጋጁ በኋላ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመውሰድ እና በማሳየት ተማሪዎች የሞዛይክን ትርጉም ቀለል ባለ መንገድ መረዳት እንዲችሉ ግለጽላቸው፡፡ በተግባር 2.2.1. ላይ እንደተሰጠው መልሱን ከዚህ በታች እንዳለው ግለጽላቸው፡፡ የሞዛይክ ስራ እንደ ስነ-ኮላጅ በስዕል/ምስል/ ፣ዲዛይን እና በፓተርን እንደሚሰራበት ሆኖ ጠጣር ከሆኑ ነገሮች ላይ እንደሚሰራ አስገንዝቧቸው፡፡ ይህ ሙያ የረጅም ዘመን ታሪክ ያለው ስለሆነ በዱሮ ግዜ ቤተ-እምነቶችን እና ቤተ-መንግስት ለማስዋብ ወይም ይጠቀሙበት እንደነበረ እና ከኮላጅ ስራ በፊት እንደተጀመረ ታሪክ እንደሚገልጽ አስገንዝቧቸው፡፡ በአሁኑ ግዜ በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች ላይ እየተሰራበት መሆኑን ንገሯቸው፡፡ በሆቴሎች፣በሎጆች፣በካፌዎች እና በመዝናኛ ቦታዎች በተለያዩ ሁኔታ እየተሰራበት ነው፡፡ ከዚህ በታች ያለውን የሞዛይክ ስራ ተማሪዎች በደንብ እንዲያዩት አድርግ፡፡ ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ ከዚህ በታች ያለውን ስራ የሚመስል ተሰርቶ ያለ ከሆነ ተማሪዎቹን ጠይቃቸው፡፡ ካለ እንዴት ባለ ነገር እንደተሰራ ተማሪዎቹን ጠይቀህ ለክፍል እንዲገልጹ አድርግ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎቹ ስለ ሞዛይክ ምንነት እና ትርጉም ተረድተው ከሆነ እና ያልገባቸው ከሆነ ለማወቅ ጥያቄ ጠይቁ፡፡



የሞዛይክ ስራን የሚያሳይ ሥዕል

ተግባር 3

**ቀለም ካለው ወረቀት የሞዛይክ አሰራር ዘዴ /ስልት/**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነገሮች /ለሞዛይክ ስራ የሚረዱን ወረቀቶች/ ተማሪዎች በሚያገኙት ውስጥ ተግባሩን ወይም ድርጊቱን በግል በግል አሰራቸው፡፡ መምህር/ት ስራውን ቀድመህ አጠገባቸው ሆነህ እያሰራህ እንዲሰሩ እያሳየሀቸው ሂድ፡፡ ወደ ስራው ከመግባታቸው ወይም ከመግባትሽ በፊት ስለስራው ከዚህ በታች ያለውን የአሰራር ሂደት እንዲገነዘቡ አድርግ፡፡

## 1. የፕሮጀክት ዝግጅት

ነጭ ወረቀት አዘጋጅ ነጭ ካርቶን በነጭ ወረቀት ልክ እኩል አድርገህ ቀረጥ፡፡ ተማሪዎችህን እንደአንተ እንዲያዘጋጁ እን እንዲቆርጡ አድርግ፡፡ ማለትም ሞዛይክ እላዩ ላይ የሚሰራበት ማለት ነው፡፡

## 2. ዲዛይን ማዘጋጀት

ቀላል የዲዛይን ቅርጽ ያለው የተለያየ አበባ፣ወፍ፣አሳ፣እና አትክልት በመጠቀም ነጭ ወረቀት ላይ ብደፍ፡፡ እነሱም እንዲነድፉ አድርግ፡፡ የሰራኸን ንድፍ እና ተማሮዎች የሰሩትን ንድፍ ቀላል እና ግልጽ መሆን አለበት፡፡

## 3. እንደሞዛይክ የሚሆን ወረቀት ማዘጋጀት

በቅድሚያ የተለያዩ ቀለሞች ያላቸውን እና ቀለሙ ከዲዛይን ጋር የሚሄድ ወይም የሚስማማ አይነት ምረጥ፡፡ ተማሪዎችህንም አስመርጥ፡፡ (እነደ ሞዛይክ) ጨሌ ትጠቀምበታለህ ማለት ነው፡፤ የመረጥከውን የቀለም ቅብ ወረቀት ክብ፣አራት ማዕዘን(ሬክታንግል) አስኬር እና ሦስት ጎን እስከ 0.5 ሳ.ሜ. ወይ 1 ሳ.ሜ. ያልበለጠ በመቀነስ በመቆራረጥ አዘጋጅ፡፡ ተማሪዎችም ያዘጋጁ፡፡

## 4. ማጣበቂያ/ማያያዣ/ሙጫ

በነጭ ወረቀት/ካርቶን ላይ የሰራኸውን ዲዛይን በተመለከተ ኮላ፣ኡሁ፣ የዛፍ ሙጫ እና የመሳሰሉትን በመጠቀም የቆራረጥከውን ባለቀለም ወረቀት በተፈለገው መጠን በማጠጋገት አያያዝ፡፡ ተማሪዎችም ልክ አንተ እንደሰራኸው ይስሩ፡፡ አጣብቀህ ከጨረስህ በኋላ እንዲደርቅ አድርግ፡፡

ልምምድ 4

መምህር/ት ከዚህ ባላይ የገለጸውን የሞዛይክ አሰራር ሂደት በመከተል ተማሮዎችህ/ሽን ከአካባቢያቸው በሚገኙ ነገሮች እንዲሰሩ አድርግ፡፡ ከሰሩ በኋላ የስራው ሂደት ውስጥ ያስቸገራቸውን ነገሮች በጋራ እንዲወያዩበት እና ጠንካራና ደካማ ጎንን ማሻሻልና ማዳበር እንዳለባቸው እና እንዲደናነቁ አድርግ፡፡ በመጨረሻም ገንቢ ሀሳብ ስጧቸው፡፡

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ግዜ………………9

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት፡

ከዚህ ትምህርት ይዘት መጨረሻ ፡

1.3. ጋሻን በመጠቀም ቲያትር ያሳዩ፡፡

አልባሳት እና ጋሻን በመያዝ ቲያትር ያቀርባሉ፡፡

2. የዚህ ይዘት ዋና ነጥብ፡

አልባሳት እና ጋሻን በመያዝ ቲያትር ያቀርባሉ፡፡

3. የይዘት መግለጫ

ይህ ርዕስ ተማሪዎች አለባበስ እና ቁሶችን በመጠቀም ቲያትር እንዲያቀርቡ የሚመራ ነው፡፡ ይህም ተማሪዎችን ባቀረቡት ጭውውት ታሪክ ላይ ተመስርቶ የተኩትን ገጸ ባህሪ እውነት በማድረግ እንዲያሳዩ እርዳ፡፡ አለባበስ እና ቁሶችን በቤታችሁ እና በአካባቢያችሁ ከሚገኝ በመጠቀም ሳይጨናነቁ ቀለል ባለ መንገድ ማሳየት፡፡

4. **የመማር ማስተማር ዘዴ**

- የቡድን ውይይት
- የእርስ በእርስ ውይይት እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- በማሳየት
- መግለጫ በመስጠት
- ጥያቄና መልስ
- ፕሮጀክት
- ሙከራ
- ልምምድ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡

- የሚለማመዱበት ክፍል (የቲያትር አዳራሽ)

- የተለያዩ አልባሳትና ለልምምድ የሚሆኑ ቁሶች

**የመምህሩ ድርሻ**

- በዚህ ርእስ የተሰጠውን ድርጊት አስተምረው መግለጫ ከመስጠትዎ በፊት ተማሪዎች ቡድን እርስ በእርሳቸው እንዲወያዩ አድርግ፡፡
- የተለያዩ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚለብሱትን የልብስ አይነቶች እያጣቀስክ ልዩነታቸው ላይ እንዲወያዩ አድርግ፡፡
- ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ምን አይነት ልብስ እንደሞለብሱ ሰዎች ለስራ እና ለተለያዩ ፕሮግራሞች የሚለብሱትን የልብስ አይነቶችን በመጠየቅ ለተማሪዎች ካስረዳችሁ በኋላ ወደ መገልጫ ልትገባ ትችላለህ፡፡
- በዚህ ርዕስ ውስጥ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሀሳቦች ላይ እንዲያተኩሩ አድርግ፡፡
- የተሰጡ ድርጊቶች የግል ስራ፣የቡድን ስራ፣የክፍል ስራ፣የቤት ስራ፣እና ፕሮጀክት እንዲሰሩ ምራቸው፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ ስራ ያላቸው ሰዎች አለባበስ እንዲያዩ አድረግ፡፡
- አጭር ተውኔት ሰርተው የተለያዩ ልብስ ተጠቅመው እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡ ለምሳሌ አርሶ አደር፣ዶክተር፣እብድ እና የመሳሰሉት ሊሆኑ የችላሉ፡፡
- ተማሪዎች ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው ክህሎት በታች ከሆኑ የክለሳ ትምህርት በማዘጋጀት እርዳታ አድርጉላቸው፡፡
- ተማሪዎች ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው ክህሎት በላይ ከሰሩ መበረታታት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ነጥብ ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ ተረድቻለሁ ብለው እንዳይዘናጉነና መቀጠል እንዳለባቸው አበረታታቸው፡፡

የተግባር 5 መልስ

1. የተለያዩ ስራ የሚሰሩ ሰዎች የልብስ አይነት ተመሳሳይ አይደለም፡፡ ለምሳሌ አስተማሪ ሊያስተምር ሊያስተም ወደ ክፍል ሲገባ የደንብ ልብስ ይለብሳል፡፡ እንዲሁም አርሶ በስራ ግዜ የሚለብሰው እና መንገድ ሲሄድ የሚለብሰው ልብስ የተለያየ ነው፡፡ እንዲሁም ፖሊስ፣ወታደር፣ትራፊክ በስራ ቦታ ላይ የሚለብሱት እና ሌላ ግዜ የሚለብሱት ልብስ ይለያያል፡፡ እንገዲህ ልብሶቻቸውን እያየን ስራቸውን መለየት እንችላለን፡፡ መምህር/ት ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች ተማሪዎች ጥቂቶቹን ተክተው እንዲጫወቱ አድርግ፡፡

## የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች


- የቡድን ውይይት
- የእርስ በእርስ ውይይት እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- በማሳየት
- መግለጫ በመስጠት
- ጥያቄና መልስ
- ፕሮጀክት
- ሙከራ
- ፈተና
- ስም መጥሪያ

የምዕራፍ ሁለት መልመጃ መልስ


I. 1.እውነት  2. እውነት  3. እውነት  4. እውነት  5. እውነት  6. ሐሰት  7. እውነት  8. እውነት  9. እውነት  10. እውነት

II. 1. ሐ  2. መ  3. ለ  4. ሐ  5. ሐ  6. ለ  7. መ  8.ለ  9.ሐ


III. 1.





2.




3.



4.




5. ፓፒረስ
6. እስቴንስል

# ምዕራፍ ሦስት

# የባህል እና የታሪክ ተጨባጭ ሁኔታ

**ለዚህ ትምህርት ምዕራፍ የተሰጠው ክፍለ ግዜ…………20**

በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡

- በዚህ መዕራፍ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች የተለያየ ሙዚቃ ክሊፖችን ለይተው ያውቃሉ፡፡
- ህብረተሰቡ የሚጠበቀምበትን ውዝዋዜ ውስጥ አንድ ትገልጻለህ፡፡
- የተለያዩ ስን-ጥበባትን ያገናዝባሉ፡፡
- የዋሻ ስነ-ጥበብን ያደንቃሉ፡፡
- በስነ-ጥበብ አፈ-ታሪክን ያሳያሉ፡፡
- ተረት ተረት እና ትርክት በስነ ጥበብ ጫወታ ያሳያሉ፡፡

## መግቢያ፡

ባለፉት ምዕራፎች ውስጥ የሙዚቃ ኖታን ስም መሰየም፣ክሌፎችን መጻፍ እና መጠቀም ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ህብረተሰቡ የሚጠቀሙበትን ትማራላችሁ፡፡ በተጨማሪም የሰው ልጅ በድሮ ግዜ እንደ አሁኑ ቤት ሰርቶ መኖር ሳይጀምር በፊት ዋሻ ውስጥ ይኖሩ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡ የዋሻው አካል ጠፍጣፋ /ዝርግ/ ድንጋይ ላይ የተለያዩ የስነ-ጥበብ ስራ በመስራት ሀሳባቸውንና ስሜታቸወን ይገልጹበት ነበር፡፡ እንዲሁም የአፈ ታሪክ ምንነትን ካስተማርክ በኋላ በቃል የሚነገር ታዋቂ የአፈ-ታሪክን ወደ ስነ-ጥበብ በመቀየር የሚጽፉ ይሆናል፡፡

## የምዕራፉ ዋና ዋና ርዕሶች

3.1. ህብረተሰቡ የሚጠቀምባቸው የባህል ሙዚቃ እና የውዝዋዜ አይነቶች (7)

3.2. ታሪካዊ የስነጥበባት አይነቶች (የዋሻ ጥበባትና የቀለም ቅብ) 6

3.3. ስነ-ቃል መንገር የተሰጣ ክፍለ ግዜ (7)

# 3.1 ህብረተሰቡ የሚጠቀምባቸው የባህል ሙዚቃ እና የውዝዋዜ አይነቶች

**. ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ግዜ ብዛት.................7**

- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባው የመማር ብቃት፡
- ከዚህ ትምህርት መጨረሻ በኋላ :-
  - የባህል ሙዚቃ አይነቶችን ይለያሉ፡፡ ህብረተሰቡ የሚጠቀምበትን ውዝዋዜ ያደንቃሉ፡፡

3.1.1. የባህል ሙዚቃ ዓይነቶች

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠው የክፍለ ግዜ ብዛት.................3**

- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት የሚገባው የመማር ብቃት፡
- ከዚህ ትምህርት መጨረሻ በኋላ :-
- የባህል ሙዚቃን በመለየት ያብራራሉ፡፡
- የባህል ሙዚቃን ምንነት ይናገራሉ፡፡
- መምህር/ት የባህል ሙዚቃ አይነቶች የሚለውን ይዘት ከመጀመርህ በፊት የተሰጡትን የግንዛቤ ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩ በማድረግ የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ ከገለጽህ በኋላ በቂ ማብራሪያ ስጥ/ጪ፡፡

የትኩረት ጥያቄ

የባህል ሙዚቃ አይነቶች እነማናቸው

7. **የመማር ማስተማር ዘዴ**

- የቡድን ውይይት
- የእርስ በእርስ ውይይት እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- በማሳየት
- መግለጫ በመስጠት
- ጥያቄና መልስ
- ፕሮጀክት
- ሙከራ
- ልምምድ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡

- የሚለማመዱበት ክፍል (የቲያትር አዳራሽ)
- አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች

**የመምህሩ ድርሻ**

- ባለፈው የትምህርት ርእስ ውስጥ ስለ ክሊፎች እና የሙዚቃ ሰሌዳን ተምራችሁ ያገኛችሁትን ግንዛቤ ከለየህ በኋላ የእለቱን የትምህርት ይዘት መለየት ትችላለህ፡፡
- ተማሪዎች ስለ ባህላዊ ሙዚቃ ዓይነቶች በቡድን እንዲወያዩ አድርገህ የውይይቱን ውጤት ለክፍል እንዲያብራሩ አድርግ፡፡
- በዚህ ትምህርት ርዕስ ውስጥ የተሰጡ ድርጊቶች ላይ በፊት ያገኙትን ችሎታ እና እውቀት በመገንዘብ ሀሳባቸውን በማብራራት እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

  ማሳሰቢያ፡ መምህር/ት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙትን የባህል ሙዚቃ በማጥናት ለክፍል ዘገባ እና በድርጊት እንዲያሳዩ አድርግ/ጊ

5. ተከታታይ ምዘና፡-

   - ከመጀመሪያዎቹ ድርጊቶች እና ጥያቄዎች ውስጥ የተወሰኑትን የክፍል እና የቤት ስራ እንዲሰሩ አድርግ፡፡
   - ለስራቸው በቂ የሆነ ገንቢ ሀሳብ በጊዜው መስጠት ይገባሃል፡፡
   - ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉጽ ከሚገባቸው ብቃት በላይ የሰሩትን ማበረታታት ይገባል፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ ሁሉንም አውቄያለሁ ብለው እንዳይዘናጉ እና ችላ እንዳይሉ በርትተው እንዲሰሩ መበረታት አለባቸው፡፡ ተማሪዎቹን ድርጊት አንድ በአንድ መዝግበህ በሰነድ መልክ ያዝ፡፡
   - ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት የሚገባቸው ብቃት በታች የሚሰሩትን ተማሪዎች በተጨማሪ መበረታታት /እገዛ/ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በትርፍ ግዙ ከትምህርት ውጪ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲማሩ አድርግ፡፡

     **ማሳሰቢያ፡-** መምህር/ት በአካባቢያችን የሚገኙ ብዙ የባህል ሙዚቃ አይነቶች አሉ፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው በመጠየቅ እና በመገንዘብ በድርጊት 1 እና 2 መሰረት እንዲዘግቡ እና እንዲያሳዩ አድርግ፡፡

**የድርጊት 1/አንድ/ መልስ፡-**

- ከሰርግ ዘፈን ውስጥ ሙሽራው/አግቢው/ ወደ ሚሽራዋ ቤት ሲሄድ በአካባቢያቸው ምን ተብሎ እንደሚዘፈን የቤት ስራ በመስጠት ጠይቀው እንዲመጡ እና ለክፍል እንዲገልጹ አድርግ፡፡

**የድርጊት ሁለት/2/ መልስ፡-**

- ሴት ልጅ ስትወልድ የሚዘፈን ዘረን ቤተሰባቸውን ጠይቀው እንዲመጡ እና ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

## 3.1.2. የባህል ውዝዋዜ አይነቶች

1. ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ……………………..4
2. ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት፡

ከዚህ ትምህርት መጨረሻ በኋላ

- የኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ አይነቶች ለይተው ይገልጻሉ፡፡
- የአካባቢያቸውን ውዝዋዜ በተግባር ያሳያሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ/ስልት/**

- የቡድን ፣የጥንት ፣ ሙሉ ክፍል ውይይት
- ገላጻ
- ጥያቄና መልስ
- ልምምድ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡**

የዚህን ትምህርት ርዕስ ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሳረያዎች፡፡

- የመለማመጃ ክፍል
- አልባሳት

**የመምህሩ ድርሻ**

- ባለፈው የትምህርት ርእስ ውስጥ ስለ ባህል ሙዚቃ ተማሪዎች ያገኙትን ግንዛቤ ከለየህ በኋላ የእለቱን የተምህርት ይዘት ማስጀመር ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ስለ ባህላዊ ውዝዋዜ በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ ውጡቱን /የደረሱበትን/ ሀሳብ ለክፍል እንዲገልጹ አድርግ/ጊ፡፡

- በእነዚህ ትምህርት ርዕሶች ውስጥ ከተሰጡት ድርጊቶች ያገኙትን ችሎታ እና እውቀት በመገንዘብ ወደ ገለጻ ከመግባትህ በፊት ለማበረታታት ያልገባቸው ነገር ካለ በቡድን እንዲወያዩ እና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አድርግ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

ከመጀመሪያዎቹ ጥያቄዎች እና ድርጊቶች የተወሰኑትን በክፌል እና በቤት ስራ መልክ እንዲሰሩ አድርግ/ጊ፡፡

ለሰሩት ስራ ትክክለኛ የሆነ ገንቢ ሀሳብ በጊዜ ስጣቸው፡፡

- ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉጽ ከሚገባቸው ብቃት በላይ የሰሩትን ማበረታታት ይገባል፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ ሁሉንም አውቄያለሁ ብለው እንዳይዘናጉ እና ችላ እንዳይሉ በርትተው እንዲሰሩ መበረታት አለባቸው፡፡ ተማሪዎቹን ድርጊት አንድ በአንድ መዝግበህ በሰነድ መልክ ያዝ፡፡
- ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት የሚገባቸው ብቃት በታች የሚሰሩትን ተማሪዎች በተጨማሪ መበረታታት /እገዛ/ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እነዘህ ተማሪዎች በትርፍ ግዙ ከትምህርት ውጪ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲማሩ አድርግ፡፡
- መምህር/ት ተማሪዎች ድርጊት ሶስት/3/ በቡድን በቡድን ሆነው በድርጊት እንዲያሳዩ ሁኔታውን አመቻች/ቺ፡፡

  የድርጊት ሦስት /3/ መልስ

  በዚህ ድርጊት ውስጥ ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው የአካባቢያቸውን የባህል ውዝዋዜ በድርጊት/በተግባር ለክፍል እንዲያሳዩ አድርግ/ጊ፡፡

# 3.2 ታሪካዊ የስነጥበባት አይነቶች (የዋሻ ጥበባትና የቀለም ቅብ)

## 3.2.1 የዋሻ ስነጥበባት

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ ተሰጠው ክፍለ ግዜ…………6**

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉ የሚገባቸው ብቃት፡

- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ
- የዋሻ አርት ፍቺ /ትርጉም/ ይናገራሉ፡፡
- የሰው ልጅ በድሮ ዘመን ዋሻ ውስጥ ሲኖር በነበረበት ዘመን ምን ምን ዓይነት ጥበባት እንደተሰሩ ይናገራሉ፡፡

የመማር ማስተማር ዘዴ /ስልት/

- የቡድን፣የጥንድ እና በሙሉ ክፍል ውይይት
- ማስመሰል
- በማሳየት
- በመለማመድ
- ጥያቄና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ ዘዴ/ስልት
- ገለጻ
- ጥያቄ እና መልስ

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

የዚህ ትምህርት ርእስ ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መረጃ መሳሪያዎች

የመለማመጃ ክፍል

ሥዕል /ምስል/

ፖስተር

**የመምህር/ት ድርሻ**

- መምህር/ት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለ ሚገኝ ዋሻ ከዚህ በፊት ጠይቀው ያገኙትን ግንዛቤ እንዲገልጹ በማድረግ ይህንን ምዕራፍ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ስለ ዋሻ ምንነት እና ፍቺ/ትርጉም/ በየግል ከሰሩ በኋላ በቡድን በቡድን እንዲወያዩበት አድርግ፡፡

- የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን አመቻች፡፡
- በንዑስ ርእሶች ስር የተሰጡት ተግባራት ተማሪዎች ቀደም ሲል የነበራቸውን ችሎታ እና እውቀት በመገንዘብ እና ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚያገለግል ከመግባትዎ በፊት በቡድን ተወያይተው ሃሳባቸውን ለተማሪዎች እንዲገልጹ ካደረክ ተማሪዎቹ እንዲነሳሱ ያደርጋቸዋል፡፡
- ከመጀመሪያዎቹ ተግባሮች እና ጥያቄዎች ውስጥ የተወሰኑትን ለክፍል ስራና ለቤት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ትችላለህ፡፡
- ተማሪዎች ለሰሯቸው ስራዎች ትክክለኛ ሀሳብ በጊዜው መስጠት አለብህ፡፡ አንተ በምታስተምርበት ክፍል ውስጥ ከሚፈለገው ችሎታ በላይ የሚሰሩ ከሆነ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ በጣም አውቄያለሁ እችላለሁ ብለው መሻሻል እንዳይቀንሱ እና በጉብዝና መቀጠል መጨመር እንዳለባቸው በርትተው እንዲሰሩ ማበረታታት እና መከታተል ያስፈልጋል፡፡
- ተማሪዎች ከተፈለገው ችሎታ በታች ከሆኑና ከሌሎች ተማሪዎች ዝቅ ብለው ከተገኙ ተጨማሪ እርዳታ እና ክትትል ያስፈልጋቸዋል፡፡ የተለየ ትኩረት እና ተጨማሪ እገዛ በትርፍ ግዜያቸው ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የእየአንዳንዳቸውን ስራና ተግባር መዝግብ፡፡ የማትመዘግብ ከሆነና የሰሩት ተግባር የማይታይላቸው ከሆነ ስራቸው ዋጋ እንደሌለው በመቁጠር እየሰነፉ ይሄዳሉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- የግል እና የቡድን ጽብረቃ
- ፖርትፖሊዮ/ዘገባ/
- የቃል ጥያቄ
- ሙከራ
- ፈተና
- የግል እና የቡድን ፕሮጀክት

የውይይት መልስ

ማሪዎች በአካባቢያቸው ዋሻ አይተው እንደሚያውቁ ጠይቃቸው

- አይተው የሚያውቁ ከሆነ ዋሻ ምን እንደሆነ በቡድን ውይይታቸው እንዲያብራሩ አድርግ፡፡ እንዲሁም በአከባቢያቸው ታዋቂ ዋሻ ካለ ስለ ዋሻው በቡድን ተወያይተው ለቡድናቸው እንዲገልጹ አበረታታ፡፡ በአካባቢያቸው የሚገኘው ዋሻ

ተነስተህ የዋሻ ጥበብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከዚህ በታች እንዳለው አስገንዝባቸው፡፡ ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን በአካባቢያቸው ታዋቂ የሆነ ወሻ ካለ ጠይቃቸው፡፡ የሚያውቁትን ለክፍል እንዲገልጹ አድርግ፡፡ ገለጻ ካደረጉ በኋላ ስለ ዋሻው ታሪክ የሚውቁትን ወይም የሰሙትን እንዲገነዛዘቡ አድርግ፡፡ በአጠቃላይ የዋሻን ትርጉም ምን ማለት ነው ለሚለው ከዚህ በታች እንዳለው አስገንዝባቸው፡፡ ዋሻ ማለት የድንጋይ አካል ወይም ትልቅ ዛፍ ግንድ በአንድ በኩል በር /ክፍት ቀዳዳ/ ያለው ማለት ነው፡፡ ዋሻ ማለት ትልቅ ድንጋይ ወይም የመሬት አካል በአንድ በኩል በር ወይም ቀዳዳ ኖሮት የሰው ልጅ ከድሮ ጀምሮ እንደአሁን ከፈለገው ነገር ቤት ሰርቶ ውስጡ መኖር ሳይጀምር በፊት መጠለያ አድርጎ ሲኖርበት የነበረ ማለት ነው፡፡

የዋሻ ጥበብ ማለት በድሮ ግዜ በዋሻ ግድግደዎች ላይ ሲሰሩ የነበሩ ስዕሎች ምስሎች ማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ ከድሮ ጀምሮ ፍላጎቱን፣ስሜቱን፣ሀሳቡን እና የመሳሰሉትን በጥበብ ሲገልጽ እንደኖረ ታሪክ ይገልጻል፡፡ ለዚህ ደግሞ ምስክር(ማረጋገጫ) የሚሆን የዋሻ ጥበብ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከድሮ ጀምሮ ዋሻ ውስጥ ሲኖር የዋሻው አካል ላይ በቀለም ቅብ የተለያዩ ምስሎችን (ስዕሎችን) ይሰሩ የበሩት የዋሻ ጥበብ ይባላል፡፡ ከዚህ በታች ያለውን በድሮ ግዜ ዋሻ ውስጥ ተሰርተው የነበሩ ከተማሪው መፅሀፍ ላይ ያለውን እይ እና የዋሻ ጥበብ በይበልጥ እንዲረዱ አድርግ፡፡

ሥዕል ገጽ 74

ውይይት 2

መምህር/ት ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ ሰዎች የሚኖሩት እነሱም የቤት ግድግዳ፣ትምህርት ቤት፣ በጤና ጣቢያ እና በመሳሰሉት ላይ ቀለም ሲቀባ አይተው የሚያውቁ ከሆነ ጠይቃቸው፡፡ አይተው የሚያውቁ ከሆነ እንዴት እንደሚቀባ በጥንድ ወይም እንደ አቀማመጣቸው እንዲወያዩ አድርግ፡፡ የተወያዩትን ለክፍል እንዲገልጹ ካደረግህ በኋላ በአጠቃላይ ሀሳብ ስለቀለም ቅብና ምንነት እነደከዚህ በታች እንዳለው ግብረ መልስ ስጣቸው፡፡

- የቀለም ቅብ የሰው ልጅ ከድሮ ዘመን አንስቶ ሀሳቡን፣ምኞቱት፣ስሜቱን እና አኗኗሩን ሲገልፅበት ከኖረ አንዱ መሆኑን በአካባቢያቸው የሚኖሩ ተፈጥሯዊ እና

ሰው ሰራሽ ነገሮችን በተለያዩ ቀለማት በመታገዝ የሚሰራበት ነው፡፡ የቀለም ቅብ ስራ ከቀለም ቅብ ስራ የሚለየው በቀለም ታግዞ በመሰራቱ ነው፡፡

- የቀለም ቅብ ስራ ከተለያዩ ነገሮች ላይ መሰራት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የውሃ ቀለም እና የዘይት ቀለም እና የመሳሰሉት ይሰራል፡፡ የቀለም ቅብን ለመስራት የሚያገለግሉ ቀለማት በፈሳሽ እና በጠጣር መልክ የሚሰሩ ናቸው፡፡

## 3.3 አፈ-ታርክ መንገር

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ግዜ……………….7**

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች

- አፈ-ታሪክን በትያትር ታሳያላችሁ፡፡
- ተረት ተረት እና ትርክትን በቲያትር ተውኔት ያሳያሉ፡፡

**የዚህ ርዕስ አንኳር ነጥቦች**

- ጌረርሳ
- ተረት ተረት
- ትርክት
- እንቆቅልሽ
- መዝሙር
- ምሳሌያዎ አነጋገር

**የይዘት ገለጻ**

አፈ-ታሪክ በንግግር መልክ የሚቀርብ ሆኖ ዜማ ተሰጥቶበትም ሆነ ሳይሰጥበት ሊቀርብ የሚችል የፈጠራና የስነ-ጥበብ አካል ሆኖ በተለያዩ የማህበረሰብ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ አፈ-ታሪክ ማለት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የህዝቡ ፈጠራ ሆኖ በንግግር መልክ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፎ የመጣ ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ባህሉን ሃይማኖቱን፣ፍልስፍናውን፣ታሪኩን፣ስነ-ምግባሩን እና እሴቱን በንግግር መልክ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ነበር፡፡ አሁንም እያስተላለፈ ነው፡፡ ይህ አፈ-ታሪክም በተለያየ ክፍል ይከፈላሉ፡፡

እነሱም፡ ጌረርሳ፣እንቆቅልሽ፣ምሳሌያዎ አነጋገር፣ተረት ተረት፣ትርክት፣መዝሙር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በተውኔት ጽሁፍ መልክ የቀረበ ተረት፡

**ሶስት ሰዎች**

በድሮ ጊዜ ሶስት ሰዎች የአንድ ሰውዬን ልጅ ሊያገቡ ሰው ላኩበትአንዱ ብልጥ ሁለተኛው ጀግና ሦስተኛው ደገሞ ፈሪ ነበር፡፡ ልጁን ለጋብቻ የተጠየቀው ሰውዬ የሀሩን ሽማገሌዎች ጠርቶ ልጅቷን ለማን እንደሚድር አማከራቸው፡፡ ሽማግሌዎቹም

ተራበተራ ሀሳባቸውን አቀረቡ፡፡ አንደኛው ሰውዬ ልጅህን ለጀግናው ሰወዬ ዳራት አለ፡፡ ሌላኛው ግን ልጅህን ለጀግናውም ለፈሪውም አትዳራት ለብልጡ ሰውዬ ዳራት አለው፡፡ ጀግናው ጀግንነቱን አምኖ ስለሚዋጋ እንደአጋጣሚ ሊሞት ይችላል፡፡ ፈሪውም ለሁሉ ሰው ይሰግዳል፡፡ ብልጡ ግን ሁለኑም ነገር በብልሃት ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ልጅህን ለብልጡ ሰውዬ ዳራት ብሎ ስበሰባቸውን ጨረሱ ይባላል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ /ስልት/**

- የቡድን፣የጥንድ እና በሙሉ ክፍል ውይይት
- ማስመሰል
- በማሳየት
- በመለማመድ
- ጥያቄና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ ዘዴ/ስልት
- ገለጻ
- ጥያቄ እና መልስ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

የዚህ ትምህርት ርእስ ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መረጃ መሳሪያዎች

የመለማመጃ ክፍል

የተለያዩ አልባሳት እና ለቲያትር የሚሆኑ ቁሶች

**የመምህር/ት ድርሻ**

- በዚህ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች የአፈ-ታሪክ ምንነት እርስ በእርሳቸው እንዲነጋገሩ በማድረግ በተማሪዎች ውይይት የመማር ማስተማር ሂደትን መጀመር ትችላለህ፡፡ የኦሮሞ አፈ-ታሪክ እና ጌረርሳ፣ ተረት ተረት፣ እንቆቅልሽ እና የመሳሰሉትን እርስ በእርሳቸው እንዲነጋገሩ እና እንዲወያዩበት አድርግ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ፡-
- ተማሪዎች መጽሀፍ ውስጥ ተጽፎ ያለውን ጌረርሳ በክፍ ውስጥ እንዲተውኑ አድርግ፡፡ ይህን ሲያደርጉ ከጎን ያለውን ክፍል እንዳይረብሹ የተማሪዎችን ድምጽ ተቆጣጠር፡፡
- ተማሪዎች መጻፍ ላይ ያለው ተረት ተከፋፍለው በቲያትር መልክ እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

- ይህ ግዜ ስለሚወስድ ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ሁኔታ አመቻችላቸው፡፡ ስለዚህ የሚሰሩትን ነገር ነጥብ መያዝ ትችላለህ፡፡
- የተሰጡት ተግባር እና ስራዎችን የግል ስራ፣የጥንድ ስራ፣የቤት ስራ፣የቡድን ስራ እና ፕሮጀክት እንዲሰሩ እና እነዲያከናውኑ ለማድገር ማጠቃለያ ግብረ መልስ ስጣቸው፡፡
- ተማሪዎች ለሰሯቸው ስራዎች ትክክለኛ ሀሳብ በጊዜው መስጠት አለብህ፡፡ አንተ በምታስተምርበት ክፍል ውስጥ ከሚፈለገው ችሎታ በላይ የሚሰሩ ከሆነ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ በጣም አውቂያለሁ እችላለሁ ብለው መሻሻል እንዳይቀንሱ እና በጉብዝና መቀጠል መጨመር እንደለባቸው በርትተው እንዲሰሩ ማበረታታት እና መከታተል ያስፈልጋል፡፡
- ተማሪዎች ከተፈለገው ችሎታ በታች ከሆኑና ከሌሎች ተማሪዎች ዝቅ ብለው ከተገኙ ተጨማሪ እርዳታ እና ክትትል ያስፈልጋቸዋል፡፡ የተለየ ትኩረት እና ተጨማሪ እገዛ በትርፍ ግዜያቸው ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የእየአንዳንዳቸውን ስራና ተግባር መዝግብ፡፡ የማትመዘግብ ከሆነና የሰሩት ተግባር የማይታይላቸው ከሆነ ስራቸው ዋጋ እንደሌለው በመቁጠር እየሰነፉ ይሄዳሉ፡፡

የተግባር አራት መልስ

አፈ-ታሪክ ማለት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በአፍ ንግግር ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የህዝብ የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ዘመናዊ የመማር ማስተማር ሥርዓትን ሳይጀምር በፊት ችሎታውንና ማንነቱን በአፈ-ታሪክ እያስተላለፈ፣እየተማመረ፣እንዲሁም ማንነቱን ለዓለም ሲገልጽ ነበረ፡፡ ዛሬም እየገለጸ ነው፡፡

የኦሮሞ ህዝብ በአፈ-ታሪኩ በአል፣ሀይማኖት፣ፍልስፍና፣ታሪክ፣ስነ-ምግባር እና እሴቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ነበር፡፡ እንዲሁም ማንነቱን ለአለም ሲገልጽ ነበር ዛሬም እየገለጸ ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ በአፈ-ታሪኩ ባህልን፣ሀይማኖትን፣ፍልስፍናን፣ታሪክ፣ ስነ-ምግባር እና እሴትን ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ነበር፡፡ እንዲሁም አሁንም እያስተላለፈ ይገኛል፡፡

ይህ አፈ-ታሪክ የተለያየ እይነት አለው፡፡ እነሱም ጌረርሳ፣ ተረት ተረት፣ እንቆቅልሽ እና የመሳሰሉትን ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ በጥልቀት መገንዘብ ያለብን ነገር የአፈ-ታሪክን ምንነት ማስተማር ብቻ ሳይሆን የአፈ-ታሪክ አይነቶችን አንዱን ወስደው በትያትር መልክ ቀይረው ተማሪዎች እንዲሳተፉበት ነው፡፡ በስነ-ጥበብ ስራዎች ውስጥ የሁሉም ነገር መሰረት የነው ሕዝብ ነው፡፡ አፈ-ታሪክ ደግሞ ከህዝቡ ንብረት አንዱ ስለሆነ

ተማሪዎች ከአፈ-ታሪክ ጥቂቶቹን በመውሰድ ማንነታቸውን ተምረው እንዲያስተምሩ የቀረበ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ከሚያውቁት አፈ-ታሪኮች መርጠው በመውሰድ ሀሳቡን ወደ ቲያትር ቀይረው እንዲያቀርቡ እና እንዲማሩበት የሚጠቁም ነው፡፡ መምህር/ት ተማሪዎች የሚያውቁትን አፈ-ታሪክ ወስደህ በቲያትር ቀይረህ ተካፋይ ሆነው እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪዎች መጻፍ ላይ የተሰጠውን ተረት መውሰድ ይቻላል፡፡

የመምህሩ ድርሻ

- በዚህ ተግባር ውስጥ ጥያቄ እንደተነሳ በማህበረሰቡ ውስጥ ጉዳት እያመጡ ያሉትን ነገሮች በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲወያዩበት በማድረግ ጀምር፡፡
- በማህበረሰቡ ውስጥ ጉዳት እያመጡ የነበሩት ችግሮች እንዴት እንደነበር እንዲገልጹ አድርግ፡፡
- የቡድኑን ውይይት ውጤት እርስ በእርሳቸው እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡
- ቲያትርን ተጠቀመው ማህበረሰብን ማስተማር እንዲችሉ ጠቁማቸው፡፡
- እለት እለት የማህረሰቡን አኗኗር እንዲጎበኙ አድርግ፡፡
- የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቀዎች የጥንድ ስራ፣የቡድን ስራ፣የክፍል ስራ፣የቤት ስራ እና ፕሮጀክት እንዲሰሩ እና እንዲያከናውኑ ማጠቃለያ ግብረ-መልስ ስጣቸው፡፡

ተከታታይ ምዘና

- የቡድን ፣የጥንድ፣የክፍል ውይይት
- የግል እና የቡድን ትወና
- ጥያቄና መልስ
- የቤት ስራ
- ሙከራ
- ፈተና
- የተማሪዎች ስም መጥሪያ

**የተግባር አምስት መልስ**

በተማሪዎች መጻፍ ላይ ያለውን ጌረርሳ እና ተረት ተረት እርስ በእርሳቸው እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ጌረርሳ ስተውኔ ሌሎች የትምህርት ክፍሎችን እንዳይረብሹ ተቆጣጠሩ፡፡

የምዕራፍ 3 የመልመጃ መልሶች

I. 1.እውነት 2. እውነት 3. ሐሰት 4.ሐሰት 5. እውነት

II. 1. መ 2. ለ 3.ሐ

III. 1. ሰ 2.መ 3.ሐ 4. ለ 5. ሀ

IV. 1. አርት/ጥበብ/ 2.እንሰሳት 3. ዶሮ እና ሶፉመር ዋሻ

# ምዕራፍ አራት

## የስነ-ጥበባት መስብነት

ስነ-ጥበባትን ማስታወቅ

**ለዚህ ምዕራፍ የተመደበው ክፈል ግዜ**……………….22

ከዚህ ትምህርት ምዕራፍ የሚጠበቀው ውጤት፡

ከዚህ ትምህርተ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ፡

የተለያዩ የእጅ ስራ ስነ-ጥበብን ያውቃሉ፡፡

ስነ-ጥበባትን በመጠቀም የሀሳብ ልዩነትን እና ተመሳሳይነትን በመለየት ትገነዘባለህ

- በስነ-ጥበባት ጥቅም ሀሳብ በመግለጽ ውስጥ ያለውን ልዩነት እና ተመሳሳይነት ትገነዘባለህ፡፡
- የእጅ ጥበብን ጥቅም ይለያሉ፡፡
- **መግቢያ፡-**
- ባለፉት ምዕራፍ ውስጥ ህብረተሰቡ ሲጠቀምበት የባህል ሙዚቃ አይነቶች እና ውዝዋዜ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የስነ-ጥበባትን ሀሳብ ተመሳሳይነት እና ልዩነት ላይ በመመረኮዝ የሚሰጠውን ገለጻ በስፋት ይማራሉ፡፡ በተጨማሪም የእጅ ጥበብ ታሪክ ይማራሉ፡፡ የእጅ ጥበብ ታሪክ ብንመለከት ረጅም እድሜ ያለው እና የሰው ልጅ ከደሮ ዘመን ጀምሮ ኑሮወን ለማሻሻል እና አመቺ ለማድረግ የተለያዩ የጥበብ ስራን ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ የእጅ ጥበብ ስራ ጥበብ በይበልጥ በአካባቢያችን ከሚገኙ ነገሮች ላይ የሚሰራ እና በስፋት በተለያዩ ስራዎች የሚሰራ መሆኑን ትማራለህ፡፡
- **የምዕራፉ ትልልቅ ይዘቶች**

4.1. በስነ-ጥበባት የሚገለፅ ሀሳብ ተመሳሳይነት እና ልዩነት

4.2. በህብረተሰቡ ውስጥ የስነ-ጥበብ እና የእጅ ጥበብ ጠቃሚታዎች

# 4.1. የስነ-ጥበብ ሀሳብ ተመሳሳይነት እና ልዩነት

***ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ግዜ................11***

. ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት፡

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት ርዕስ መጨረሻ በኋላ :

የስነ-ጥበባትን በመጠቀም ሀሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ /ስልት/**

- የቡድን፣የጥንድ እና በሙሉ ክፍል ውይይት
- ማብራሪያ መስጠት
- ገለጻ
- በማሳየት
- በመለማመድ
- ጥያቄና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ ዘዴ/ስልት
- ሙከራዎች
- ጥያቄ እና መልስ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

የዚህ ትምህርት ርእስ ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መረጃ መሳሪያዎች

- ሠንጠረዘገሮች/ቻርቶች/
- ምስሎች/ስዕሎች/
- ፖርተሮች
- ሞዴሎች

**የመምህር/ት ድርሻ**

- ተማሪዎች የባህል ሙዚቃ አይነቶች እና ውዝዋዜ እንዲሁም የስነ-ጥበብ ታሪክ ውስጥ የሚገኙትን እና አፈ-ታሪክ በባለፈው ምዕራፍ ትምህርት ላይ ያላቸውን ግንዘቤ ከለየህ በኋላ ይህን ይዘት ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች የስነ-ጥበባት ሀሳብ ተመሳሳይነት እና ልዩነት በቡድን እንዲወያዩበት አድርገህ የውይይቱን ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

- በንዑስ ርዕሶች ስር የተሰጡት ተግባሮች ቀደም ሲል የነበራቸውን ችሎታ እና አውቀት ለመገንዘብ እና ለማበረታታት ስለሚረዱ ወደ ገለጻ ከመግባትህ በፊት በቡድን ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አድርግ፡፡

## 2. ተከታታይ ምዘና

- ከበፊቱ ተግባራት እና ጥያቄዎች ውስጥ የተወሰኑትን በክፍል እና በቤት ስራ እንዲሰሩት ማድረግ፡፡
- ለሰሩት ስራ በቂ ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት አለብህ፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጾፉ የሚገባቸውን ብቃት ከዚህ በላይ ለሰሩት መበረታት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ በደንብ አውቄያለሁ ብለው እንዳይዘናጉ ማበረታታት እና በጥንካሬ እንዲሰሩ ሰርተው ከስንፍና እንዳይገቡ መርዳት፡፡ የተማሪዎችን ተግባር አንድ በአንድ መዝግብ፡፡
- ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው ብቃት በታች እንዳይሰሩ እና ሌሎች ጎበዝ ተማሪዎች ላይ እንዲደርሱ ተጨማሪ ትምህርት በትርፍ ጊዜ ትኩረት በመስጠት ማገዝ ያስፈልጋል፡፡

**የተግባር አንድ መልስ**

*መምህር/ት ተማሪዎች በተግባር አንድ/1/ ላይ የተወያዩበትን ለክፍል እንዲገልጹ ሁኔታውን አመቻች፡፡ የስነ ጥበባትን ሀሳብ በጥንድ ሆነው ተመሳሳይነታቸውን እና ልዩነታቸውን ለክፍል እንዲገልጹ አድርግ፡፡*

➢ **የይዘቱ ማብራሪያ**

ንባብ ከህብረተሰብ ባህል ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በጥበብ ፈጠራ ሀሳባችንን እና ራዕያችንን እንገልጽበታለን፡፡ ይህም ጥበብ የተለያዩ ክፍሎችን ይዟል፡፡

**እነርሱም**፡- ስነ-ጥበብ፣ሙዚቃ፣ሥነ-ፅሁፍ፣ሥነ-ቲያትር፣ስነ-ፊልም እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ጥበብ በጊዜ /ሰአት/ የሚወሰን /የሚገደብ/ አይደለም፡፡

- ያለፈ ጉልበት /ሀይል/ አሁን ሊኖር የሚችል ነው፡፡ ጥበብ ብሔርን/ህብረተሰብን ወደ አንድነት ያመጣል፡፡ ይህም ማለት ጥበብ ህብረተሰብን በመለወጥ ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው ማለት ነው፡፡ ማንኛውም

ጥበብ የተፈጠረው የአንድን ህብረተሰብ ኑሮ ወደ አንድ የተሸለ ወይም ወደ መልካም ለመለወጥ ጥበብ ሁልጊዜ ከህብረተሰብ ተነጥሎ መኖር አይችልም፡፡

- ስነ-ጥበባትን በመጠቀም ለምኞት እና ለራስ ፍላጎት እንዲሁም ቋንቋ፣ባህል፣ታሪክ፣ሀይማኖት፣ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ሕብረተሰባዊነትን ለማሰደግ እና ለማበልጸግ ይቻላል፡፡ ሥነ-ጥበባት ህብረተሰቡን ማማከል አለበት፡፡ ለመለወጥም ሆነ ሁኔታን ለመቀየር የሚችለው ከህብረተሰብ ኑሮ ጋር ነው፡፡
- ስነ-ጥበባት ከህብረተሰብ ስሜት ጋር ይያያዛል፡፡የህዝብን ሀሳብ በመለወጥ ነውርን በማስተማር በህብረተሰብ ልምድ ውስጥ የኖረ እና ትርጉም በመፍጠር ግፊት ያደርጋል፡፡ ጥበብ በህብረተሰብ እድገት ወይም ለውጥ ውስጥ እንደ ሞተር፣ፖለቲካ ወይም በህብረተሰብ ውስጥ ድምጽ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የሚፎክር በፉከራ፣የሚዘፍን በዘፈን፣ያዘነ በለቅሶ፣የተደሰተ በሳቅ፣የሚያንጎረጉር በእንጉርጉሮ፣የሚያወድስ በውዳሴ፣የተናቀ በስድብ ሀሳቡን እና የውስጥ ፍላጎቱን ይገል፡፡ በዚህ መሰረት ህዝባችን ከድሮ ጀምሮ እየተጠቀመበት መጥቶ ዛሬም እየተጠወመበት ነው፡፡ ስነ-ጥበባት ገንዘብ ለማስገኘት ይጠቅማል፡፡

# 4.2 በህብረተሰብ ውስጥ የስነ-ጥበብ እና የእጅ ጥበብ ጥቅም

## 4.2.1. የእጅ ጥበብ

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ግዜ ……………11

ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት የሚገባቸው የመማር ብቃት፡-

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ የእጅ ጥበብን ትርጉም/ፍቺ/ ይገልጻሉ፡፡**

- በሕብረተሰብ ወስጥ የሚገኙትን የእጅ ጥበብ ስራ ዓይነቶች ይዘረዝራሉ፡፡
- በሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን የእጅ ጥበብ ጥቅም ይናገራሉ፡፡
- የእጅ ጥበብ በህብረተሰብ ውስጥ ያለውን ተመሳሳይነት እና ልዩነት ምን እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ/ስልት/**

- ምልከታ
- ማሳየት
- መለማመድ
- በጥንድ፣በቡድን እና በሙሉ ክፍል ውይይት
- ገለጻ
- ጥያቄ እና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ ዘዴ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

የዚህ ርዕስ ይዘት ለማስተማር የሚየስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎች

የመለማመጃ ክፍል/ስቱዲዮ

ስዕል/ምስል

ፖስተር

**የመምህሩ/ሯ ድርሻ**

- መምህርት ተማሮዎች በህብረተሰብ ውስጥ ያለውን የእጅ ጥበብን ጥቅም በመጠየቅ ከዚህ ቀደም/በፊት/ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልጹ በማድረግ ይህን ምዕራፍ ማስጀመር ይቻላል፡፡

- ተማሪዎች በህብረተሰብ ውስጥ ላለው የእጅ ጥበብ ጥቅም በመጠየቅ በቡድን በቡድን እንዲወያዩበት አድርግ፡፡ የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል ተማሪዎቻቸው እንዲያቀርቡ ሁኔታውን አመቻች፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት ከዚህ በፊት የነበራቸውን ችሎታ እና እውቀት በመገንዘብ እና ተማሪዎች እንዲነቃቁ ስለሚረዳቸው ወደ ገለጻ ከመግባትህ በፊት በቡድን ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ካደረግህ ተማሪዎችህ እንዲነቃቁ ያግዝሃል፡፡
- ከዚህ በፊት ከተሰጡት ተግባራት እና ጥያቄዎች የተወሰኑትን በክፍል ስራ እና በቤት ስራ እንዲሰሩት ማድረግ ትችላለህ፡፡
- ለሰሩት ስራ በወቅቱ ትክክለኛወን ግብረ-መልስ መስጠት አለብህ፡፡
- አንተ በምታስተምርበት ክፍል ውስጥ ከዝቅተኛ ደረጃ በላይ የሚሰሩ ተማሪዎች ካሉ መበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው/ጉብዝናቸው/ ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ በደንብ አወቅን ብለው መሻሻል እንዳያቆሙ እና እንዳይሰንፉ በርትተው እንዲሰሩ መበረታት አለባቸው፡፡
- ከሚጠበቅባቸው ደረጃ በታች የሚሰሩ ተማሪዎችን ሌሎች ተማሪዎች እንዲደርሱባቸው ተጨማሪ እርዳት ይፈልጋሉ፡፡ ለተማሪዎቹ ትኩረት በመስጠት በተጨማሪ በትርፍ ግዜ መረዳት እና ትምህርት መስጠት ይገባል፡፡
- የእየአንዳንዱን ተማሪ ውጤት መዝግብ፡፡ ስራቸው የማይመዘገብ ከሆነ እና እንዲሰሩ የማይዝላቸው ከሆነ ሊሰንፉ እና ስራቸው ወጋ የሌለው ስለሚመስላቸው መመዝገብ ይገባል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- የግል እና የቡድን ጽብረቃ
- የፖርቲፎሊዮ ዘገባ
- ቀለ-መጠይቅ
- ሙከራ
- ፈተና
- ግልና የቡድን ፕሮጀክት ስራ

የተግባር ሁለት (2) መልስ

- የእጅ ጥበብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎችን ከጠየቅህ በኋላ በግል በግል እንዲያስቡበት አጭር ጊዜ ስጣቸው፡፡ በመቀጠልም የተማሪዎችን መልስ እና ሀሳብ ካዳመጥህ በኋላ አበረታታቸውና አጠቃላይ ሃሳብ እና ግብረ-መልስ ከዚህ በታች እንደተገለጸው አስገንዝባቸው፡፡
- የእጅ ጥበብ ማለት አስፈላጊና ውብ ውብ /ቆንጆ/ ስራዎችን ቀላል የሆኑ እቃዎችን በመጠቀም ሙሉ በሙሉ በሰው እጅ ብቻ የሚሰሩ መሆናቸውን በደንብ ግለጽላቸው፡፡
- በመጨረሻም ተማሪዎች ይህን ይዘት ተገንዝበው ከሆኑ እና ያለመገንዘባቸውን ለመለየት አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠቀም መለየት ትችላለህ፡፡

መምህር/ት ተማሪዎቹ በሚኖሩበት ህብረተሰብ የሚታወቁበት /የሚሰሩትን/ የእጅ ጥበብ በቡድን በቡድን ተወያይተውበት ለክፍል እንዲገልጹ ሁኔታውን አመቻች፡፡ እንዲሁም ምን ምን አይነት ጥበብ እንደሚሰሩና እንዴትስ እንደሚሰሩ እንዲያብራሩ አድርግ፡፡

**የምዕራፍ አራት /4/ መልመጃ መልስ**

I. 1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. ሀሰት 5. ሀሰት 6. ሀሰት

II. 1.መ 2. መ 3. መ 4.መ

# ምእራፍ አምስት

# የስነ-ጥበባት ትስስር

**ለዚህ ምዕራፍ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ግዜ……………………23**

የዚህ ምዕራፍ ውጤት፡-

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ በኋላ፡-

- የትራፊክ አደጋ፣ኤች አይ ቪ/HIV/ በሽታ፣የሰውን አእምሮ የሚያደነዝዙ ነገሮች ፣ ውዝዋዜ እና ቲያትርን በመታገዝ ያሳያሉ፡፡
- በህብረተሰብ ውስጥ ያሉትን ምልክቶች እና ወኪሎችን ይበነዘባሉ፡፡
- በህብረተሰብ ውስጥ ያሉትን ምልክቶችና ወኪሎች ያላቸውን ጥቅም ያደንቃሉ፡፡
- የቲያትር ጥበብ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለወን ጥቀም ይገልጻሉ፡፡

## መግቢያ

የትራፊክ አደጋ፣አእምሮን የሚያደነዝዝ ሱስ፣ተላላፊ በሽታዎች እንደ ኤች አይ ቪ/HIV/ የአየር መበክል፣ የደን ውድመት እና የመሳሰሉት ከዘመኑ የሚሄዱ ጉዳዮች ለሰው ልጅ የወደፊት ኑሮ አስጊ የሆኑ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም የሥነ-ጥበባት ሥራዎች ከዘመኑ ጋር የሚያያዙ ነገሮችን ለህዝብ መረጃ መስጠት፣ግንዛቤ በመፍጠር ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ይጫወታሉ፡፡ ሕብረተሰብን ከችግር ለማውጣት/ለማዳንም ሆነ የአኗኗር ሁኔታወን ለመለወጥ በተለያዩ መንገዶች ትምህርቱ ይሰጣል፡፡ ትምህርቱ የሚሰጥበት መንገድ ውስጥ አንዱ የስነ-ጥበባትን በመጠቀም ነው፡፡ ይህም ርዕስ ስነ-ጥበባትን በመጠቀም ተማሪዎች ህብረተሰብን እንዲያስተምሩ የሚመራ ነው፡፡

**የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች**

5.1. **የስነ ጥባብ ትስስር** ክፍለ ግዜ 7

5.2. መዝሙር፣ውዝዋዜ እና ቲያትር በመጠቀም ከጊዜው ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን ማስተማር ክፍለ ግዜ 9

5.3. በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምልክቶች (ሎጎና አርማ) ክፍለ ግዜ 7

# 5.1 የስነ ሥዕል ትስስር

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ.....................7**

ቢያንስ ተማሪዎች ሊያበለጽጉ የሚገባ የመማር ብቃት፡-

ከዚህ ትምህርት ርዕስ መጨረሻ በኋላ ተማሪዎች ፡

- መዝሙር፣ውዝዋዜን፣በመጠቀም ከጊዜው ጋር ህብረተሰቡ ውስጥ አስቸጋሪ ጉዳዮችን ያሳያሉ፡፤
- የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እንደ ኤች አይ ቪ/HIV/ እና ሌሎችን እና የተለያዩ የሱስ አይነቶችን በመዝሙር ያሳያሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ/ስልት**

- መለማመድ
- የቡድን ውይይት
- በጥንድ እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- ገለጻ
- ጥያቄ እና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ ዘዴ
- ሙከራ
- ማብራራት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

የዚህ ርዕስ ይዘት ለማስተማር የሚየስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎች፡

- ሰንጠረዥ/ቻርት/

- ምስልት/ስዕሎች/
- ፖስተር
- ሞዴል

**የመምህሩ/ሯ ድርሻ**

- ተማሪዎች የስነ-ጥበባትን ተመሳሳይነት እና ልዩነት ባለፈው ምዕራፍ ትምህርት ያገኙትን ግንዛቤ ከለየህ በኋላ ይዘቱን ማስጀምር ይቻላል፡፡
- መዝሙር እና ውዝዋዜ በመጠቀም ከግዜው ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን እንዴት መግለጽ እንደሚቻል በቡድን እንዲወያዩበት በማድረግ እና የውይይቱን ውጤት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት ቀደም ሲል ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ እና እውቀት በመገንዘብ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ስለሚጠቅም ወደ ገለጻ ከመግባትህ በፊት በቡድን ሆነው ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አድርግ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- ከበፊቱ ተግባራት እና ጥያቄዎች ውስጥ የተወሰኑትን በክፍል እና በቤት ስራ እንዲሰሩት ማድረግ፡፡
- ለሰሩት ስራ በቂ ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት አለብህ፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸውን ብቃት ከዚህ በላይ ለሰሩት መበረታት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ በደንብ አውቄያለሁ ብለው እንዳይዘናጉ ማበረታታት እና በጥንካሬ እንዲሰሩ ሰርተው ከስንፍና እንዳይገቡ መርዳት፡፡ የተማሪዎችን ተግባር አንድ በአንድ መዝግብ፡፡
- ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው ብቃት በታች እንዳይሰሩ እና ሌሎች ጎበዝ ተማሪዎች ላይ እንዲደርሱ ተጨማሪ ትምህርት በትርፍ ጊዜ ትኩረት በመስጠት ማገዝ ያስፈልጋል፡፡

የተግባር አንድ/1/ እና ሁለት /2/ መልስ

- መምህር/ርት ተማሪዎች ተግባረ አንድ/1/ እና ሁለት/2/ ላይ ተወያይተው ለክፍላቸው እንዲገልጹ ሁኔታዎችን አመቻች፡፡

የኤች አይ ቪ/HIV/ በሽታ መዝሙርን አስመልክቶ በአካባቢያቸው ከሚያውቁት ውስጥ አንዱን በመምረጥ እንዲለማመዱ እና ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

ስለ ትራፊክ አደጋ ተላላፊ በሽታዎችን በማስመልከት የተዘፈነ/የተዘመረ ወይም ተማሪው አዘጋጅቶ ያለው ካለ በቡድን በመሆን በውዝዋዜ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

## 5.2 ትያትርን በመጠቀም ከግዜው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ነገሮች ማስተማር

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ**…………………6

ቢያንስ ተማሪዎች ሊያበለጽጉ የሚገባ የመማር ብቃት፡-

ከዚህ ትምህርት ርዕስ መጨረሻ በኋላ ተማሪዎች ፡

- የትያትር ጥበብን በመጠቀም ከጊዜው ጋር ህብረተሰቡን የሚያስቸግሩትን ጉዳዮችን ያስተምራሉ፡፡

**የዚህ ይዘት አንኳር ነጥቦች፡-**

ትያትር በመጠቀም ከጊዘ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ማስተማር፡፡

**የይዘቱ መግለጫ**

ትያትር ለማዝናናት ብቻ ሳይሆን ለማስተማርም ትልቅ ድረሻ አለው፡፡ ተመልካቾች ቀላል በሆነ ሁኔታ እየተዝናኑበት ትምህርት ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ ያሉትን ከጊዜው ጋር የሚያያዙትን እና አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉትን በቲያትር መልክ ሰርቶ ህብረተሰቡ እንዲጠነቀቅ ማድረግ ይቻላል፡፡ በህብረተሰብ ውስጥ በተደጋጋሚ ህብረተሰቡን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮች እንደ አልኮል መጠጥ መጠጣት፣በሴቶች እና በህጻናጽ ላይ የሚደርስ ጥቃት፣የትራፊክ አደጋ፣የኤች አይ ቪ/HIV/ በሽታን እና የተለያዩ ሱሳ ሱስ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ህብረተሰቡን የሚጎዱ ከጊዜው ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች በትያትር በመጠቀም ተማሪዎች ህብረተሰቡን እንዲያስተምሩበት ምሯቸው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ/ስልት**

- መለማመድ
- የቡድን ውይይት
- በጥንድ እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- በማሳየት
- ገለጻ መስጠት
- ጥያቄ እና መልስ
- የፕሮጀክት ስራ ዘዴ/ስልት/
- ሙከራዎች

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

- የመለማመጃ ክፍል/ቲያትር ክፍል/
- አልባሳት እና የተለያዩ ነገሮች /ለቲያትር እንዲሆን/

**5. ተከታታይ ምዘና**

- የተሰጡትን ተግባራት እና ጥያቄዎች በግል፣በጥንድ፣በቡድን በቡድን፣የክፍል ስራ፣የቤት ስራ እና የፕሮጀክት ስራዎች እንዲሰሩ እና እንዲከናወኑ አድርግ፡፡
- የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፤
- የአካባቢያቸውን ህብረተሰብ ኑሮ እንዲኀበኙ አድርግ፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸውን ብቃት ከዚህ በላይ ለሰሩት መበረታት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ በደንብ አውቄያለሁ ብለው እንዳይዘናጉ ማበረታታት እና በጥንካሬ እንዲሰሩ ሰርተው ከስንፍና እንዳይገቡ መርዳት፡፡ የተማሪዎችን ተግባር አንድ በአንድ መዝግብ፡፡
- ቢያንስ ተማሪዎች ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው ብቃት በታች እንዳይሰሩ እና ሌሎች ኀበዝ ተማሪዎች ላይ እንዲደርሱ ተጨማሪ ትምህርት በትርፍ ጊዜ ትኩረት በመስጠት ማገዝ ያስፈልጋል፡፡

የተግባር 4 መልስ

1. በአካባቢያችሁ በማህበረሰቡ ላይ ከሚደርሱ ነገሮች ውስጥ አንዱን በመመርጥ በትያትር መልክ ተማሪዎቹ ኣጋጅተው እንዲያሳዩ አድርግ፡፡

# 5.3 በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉምልክቶች እና ወካዮች

## 5.3.1. አርማ እና ማስታወቂያ

**ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ…………………7**

ቢያንስ ተማሪዎች ሊያበለጽጉ የሚገባ የመማር ብቃት፡-

ከዚህ ትምህርት ርዕስ መጨረሻ በኋላ ተማሪዎች ፡

- ህብረተሰቡ ውስጥ ምልክቶችና ወካዮች ትርጉም ይገልጻሉ፡፡
- ማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የስዕል ምልክቶች እና ወካዮች ይሰራሉ፡፡
- ስለ አርማ እና ማስታወቂያ
- አርማን እና የማስታወቂያን ልዩነት ይጽፋሉ፡፡
- ህብረተሰቡ ስላለው ምልክቶች እና ወካይ ጥቅም ይገልጻሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴ/ስልት**

- መለማመድ
- በምልከታ
- በማሳየት
- በቡድን ውይይት፣በጥንድ እና የሙሉ ክፍል ውይይት
- የአፍ ገለጻ
- ጥያቄ ና መልስ
- የፕሮጀክት መልክ

**የትምህርት መርጃ መሳረያ**

ለዚህ ትምህርት ርዕስ ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሳሪያዎች፡

- የመለማመጃ ክፍል/እስቲዲዮ/
- ስዕል
- ማስታወቂያ
- አርማ
- የስዕል - ገለጻ

**የመምህሩ/ሯ ድርሻ**

መምህር/ርት ተማሪዎች ስለ ትራፊክ አደጋ ፣የሰው አእምሮ የሚያደነዝዙ ሱሶች፣ተላላፊ በሽታዎች እንደ የኤች አይ ቪ/HIV/ የአየር ብክለት ፣የደን መመንጠር እና የመሳሰሉት ከጊዜ ጋር ተያይዞ የሚጎዳቸውን ከመጠየቅህ በፊት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልጹ በማድረግ የሽኛውን የትምህርት ይዘት ማስጀመር ይቸላል፡፡

ተማሪዎች ስለ ትራፊክ አደጋ ፣የሰው አእምሮ የሚያደነዝዙ ሱሶች፣ተላላፊ በሽታዎች እንደ የኤች አይ ቪ/HIV/ የአየር ብክለት ፣የደን መመንጠር እና ስለ መሳሰሉት በቡድን እንዲወያዩ ከአደረግህ በኋላ የውይይቱን ውጤት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን አመቻች፡፡

በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጡትን ተግባራት ከዚህ በፊት የነበራቸውን ችሎታ እና እውቀት በመገንዘብ እና ተማሪዎች እንዲነቃቁ ስለሚረዳቸው ወደ ገለጻ ከመግባትህ በፊት በቡድን ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ካደረግህ ተማሪዎችህ እንዲነቃቁ ያግዝሃል፡፡

ከዚህ በፊት ከተሰጡት ተግባራት እና ጥያቄዎች የተወሰኑትን በክፍል ስራ እና በቤት ስራ እንዲሰሩት ማድረግ ትችላለህ፡፡ለሰሩት ስራ በወቅቱ ትክክለኛወን ግብረ-መልስ መስጠት አለብህ፡፡ አንተ በምታስተምርበት ክፍል ውስጥ ከዝቅተኛ ደረጃ በላይ የሚሰሩ ተማሪዎች ካሉ መበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ጥንካሬያቸው/ጉብዝናቸው/ ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ በደንብ አወቅን ብለው መሻሻል እንዳያቆሙ እና እንዳይሰንፉ በርትተው እንዲሰሩ መበረታት አለባቸው፡፡

ከሚጠበቅባቸው ደረጃ በታች የሚሰሩ ተማሪዎችን ሌሎች ተማሪዎች እንዲደርሱባቸው ተጨማሪ እርዳት ይፈልጋሉ፡፡ ለተማሪዎቹ ትኩረት በመስጠት በተጨማሪ በትርፍ ግዜ መረዳት እና ትምህርት መስጠት ይገባል፡፡

የእየአንዳንዱን ተማሪ ውጤት መዝግብ፡፡ ስራቸው የማይመዘገብ ከሆነ እና እንዲሰሩ የማይዝላቸው ከሆነ ሊሰንፉ እና ስራቸው ወጋ የሌለው ስለሚመስላቸው መመዝገብ ይገባል፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

- የግል እና የቡድን ጽብረቃ
- የፖርቲፎሊዮ /ሪፖርት/

- የአፍ ጥያቄ
- ሙከራ
- ፈተና
- ግልና የቡድን ፕሮጀክት ስራ

**የውይይት 1 መልስ**

መምህር/ት ተማሪዎቹ የተለያዩ ምልክቶችን እነደ ሀኪም ቤት፣ትምህርት ቤት፣ካፍቴሪያ መንገድ ዳር የተለጠፉ አይተው ያውቁ እንደሆነ ጠይቃቸው፡፡ አይተው የሚያውቁ ከሆነ ምን አይነት ምልክቶች እንደሆኑ እና ምን አይነት መልዕክት እንደሚያስተላልፉ በቡድን ተወያይተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲገልጹ አድርግ፡፡ ያዩትን ነገር ለክፍሉ ካስረዱ በኋላ ተማሪዎቹን በማበረታታት እነሱ በአካባቢያቸው ከሚያውቁት ነገር ላይ በመነሳት ስለ አርማና የሚያወራውን የትምህርት ይዘት ከዚህ በታች እንዳለው አስረዳቸው፡፡

አርማ ማለት፡- በምልክት በአጭር መልኩ መልእክት የሚያስተላልፍ ነው፡፡ አርማ ምልክት ወይም ወካይ እንጂ ስዕል አይደለም፡፡ ሌላው ምልክት ደግሞ ፊደልም ሊሆን ይችላል፡፡ አርማ ከስነ-ጥበብ ውስጥ አንዱ ሆኖ የትራፊክ ምልክት የ HIV /ኤች አይ ቪ እና የመሳሰሉትን በመወከል የሚገለጽ ነው፡፡

አንድ አርማ በሚሰራ ጊዜ ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ቀላል በሆነ መንገድ ማንኛውም ሰው ምልክቱን አይቶ ለመተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት በቀላሉ እንዲረዳ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት፡፡ ለምሳሌ፡- የትራፊክ ምልክት ብንወስድ ተማሪዎች መንገድ በሚያቋርጡበት ቦታ ደብተር የዘው የሚሄዱ ተማሪዎች ምልክት ተወክሎ መንገድ ዳር የሰቀላል/ይለጠፋል፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች ስለ አርማ እና ማስታወቂያ ምንነት መረዳትና አለመረዳታቸውን ለመለየት የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አረጋግጥላቸው፡፡

**ልምምድ 1**

መምህር/ት ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን የትራፊክ ምልክቶች በደንብ በማየት የትራፊክ ምልክቶችን ትርጉም ለይተው እንዲያውቁ አድርግ፡፡ ስለ ምንነቱ እና ስለ ትርጉሙ ካወቁ በኋላ በደንብ በማስመሰል እንዲሰሩ አድርጋቸው፡፡ በመቀጠልም በማዘጋጀት አስመስለው ከሰሩ በኋላ በምሳሌ ላይ ያለውን ሁሉንም ቀለማት በማየት አንድ በአንድ እንዲቀቡ አድርግ፡፡ በመጨረሻም የሰሩትን ስዕል ይዘው ተማሪዎቹ

ፊት ለፊት በመውጣት ስዕሉ ላይ ያሉትን ምልክቶች እና የትራፊክ ምልክቶች ላይ ያሉትን ቀለማት አንድ በአንድ እንዲያስረዱ አበረታታቸው፡፡

ስዕል ገጽ 98

**ውይይት 2 መልስ**

መምህር/ት ተማሪዎች የተለያዩ ስዕል/ምልክቶች እና ጽሁፎች/ ተቀናጅተው የተሰሩ ሀኪም ቤት፣ትምህርት ቤት፣ መንገድ ዳር የተሰቀለ/የተለጠፈ/ አይተው የሚያውቁ ከሆነ ጠይቃቸው፡፡ አይተው የሚያውቁ ከሆነ በስዕል እና በጽሁፍ ተቀናጅተው የተሰሩት ምን አይነት እንደሆኑና ምን አይነት መልዕክት እንደሚያስተላልፉ በቡድን ተወያይተው ለክፍሉ እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡ ያዩትን ነገር ለክፍሉ ከገለጹ በኋላ ተማሪዎቹን በማበረታታት በአካባቢያቸው ከሚያውቁት ነገር ላይ በመነሳት ስለ ማስታወቂያ ይዘት ከዚህ በታች እንዳለው አስረዳቸው/ግለጽላቸው/፡፡

**ማስታወቂያ ማለት፡-** አጭር ጽሁፍ እና ስዕል ተቀናጅቶ ሙሉ የሆነ መልእክትና ግልጽ የሆኑ መልእክት ለማህበረሰቡ እንዲያስተላልፍ የሚታተም ወይም የሚሰራ ነው፡፡ ጽሁፉም ሆነ ስዕሉ የሚያምር ሆኖ ሰዎችን በሚስብ መልኩ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡ የስራውም ሁኔታ እንዲሁም በቀላሉ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ማስተላለፍ እንዲችል ተደርጎ መሰራት እንደለበት አስረግጠህ አስገንዝባቸው፡፡

**ስዕል ገጽ 99**

**ተግባር 5**

መምህር/ት በተማሪዎች አካባቢ መንገድ ዳር የተለጥፎ ነገሮች እና አይተዋቸው የሚያውቁትን የይዘቱን መልዕክት አርማ እና ማስታወቂያ ከተማሩ በኋላ ማስታወቂያ ወይም አርማ መሆኑን እንዲለዩ አድርግ/ጊ፡፡

የምእራፍ 5 መልመጃ መልስ

መመሪያ I.

| | | |
|---|---|---|
| 1. ሐሰት | 5. ሐሰት | 9.እውነት |
| 2. እውነት | 6. እውነት | |
| 3. ሐሰት | 7. እውነት | |
| 4. እውነት | 8. ሐሰት | |

*መመሪያ* I.

1. *መ* 2. *መ*

3. **ለ** 4. *መ*

5. *መ* 6. *መ*

# የሥነጥበባት ትምህርት ሲለበስ

# አምስተኛ ክፍል

# የስነጥበባት ትምህርት ሲለበስ አምስተኛ ክፍል

**የመማር ዉጤቶች፡**

**በዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች:-**

- የስነጥበብ አላባዊያን (መስመር፣ ቅርጽ፣ ገጽታ፣ ቀለም፣ እሴት፣ አቀማመጥ) ቲአተር፣የምስለ-ድምፅ አቀራረጽ ዘዴ፣ ሙዚቃ (ምት፣ ዳይናሚክስ፣ ቴምፖ፣ ፒች...) ዉዝዋዜ (dance) ይለያሉ፤
- ቀላል የሙዚቃ ኖታዎችን ያነባሉ፤
- የብሎክ ህትመትና የሞዛይክ ስራ ወረቀት ላይ ያዘጋጃሉ፤
- አልባሳትንና መሳሪያዎችን በመጠቀም ቀለል ያለ ትያትር ያሳያሉ፤
- የሀሳብ መመሳሰልንና መለያየትን በስነጥበብ ያሳያሉ፤
- ስነጥበብና እጅጥበብ በማህበረሰብ ውስጥ ያለዉን አገልግሎት ይረዳሉ፤
- ዜማ፣ ዉዝዋዜና፣ ቲአተርን በመጠቀም የትራፊክ አደጋ፣ የኤችአይቪ በሽታ፣ አደንዛዥ ዕጾች (ወቅታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ) እና የመሳሰሉትን ያሳያሉ፤
- በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምልክቶችን (ማስታወቂያ እና አርማ) ይለያሉ፤
- ባህላዊ ዘፈንና ዉዝዋዜን ይለያሉ፤
- በታሪክ ውስጥ የሚገኙ የስነጥበብ አይነቶችን ይለያሉ (የዋሻ ስነጥበብና ቀለም ቅብ)
- በማህበረሰቡ ዉስጥ የሚገኙ የስነጥበብ ስራዎችን በዜማ፣ በዉዝዋዜ፣ በቲአተርና ድምጽ አልባ ትወና/ፓንቶማየም ያሳያሉ
- በማህበረሰቡ ዉስጥ ውስጥ ባህላዊ ሙዚቃና ዉዝዋዜ ይለያሉ
- የተመለከቷቸዉን ነገሮች በቃል ይግለጻሉ

| የትምህርት ዐበይት ነጥቦች | ይዘት | የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች | ምዘናና ክትትል |
|---|---|---|---|---|
| ስነጥበባትን መረዳት | **ምዕራፍ** 1:<br>1. የስነጥበባት አላባውያን PVA (ክፍለ ጊዜ 24 )<br>1.1. የትዕይንት አላባውያን (መስመር፣ ቅርጽ፣ ገጽታ፣ ቀለም፣ እሴት፣ አቀማመጥ) (ክፍለ ጊዜ 5)<br>1.2. የሙዚቃ አላባውያን (ምት፣ ዳይናሚክስ፣ ቴምፖ፣ ፒችና የመሳሰሉት). (ክፍለ ጊዜ 5)<br>1.3. የውዝዋዜ አላባውያን (ክፍለ ጊዜ 5)<br>1.4. የትያትር አላባውያን (መቼት፣ ቃለ-ምልልስና የመሳሰሉት). (ክፍለ ጊዜ 5)<br>1.5. ቀላል የምስለ-ድምፅ ወይም የቪዲዮ አቀራረጽ ዘዴዎች (ክፍለ ጊዜ 4) | ☞ ትዕይንትና ልምምድ | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ክራውንና የመሳሰሉት<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ<br>▪ የተለያዩ ጽሁፎች | ▪ ምልከታ<br>▪ የግል ገለፃ<br>▪ የቡድን ገለፃ<br>▪ ፖርትፎሊዮ<br>▪ የቃል ጥያቄ<br>▪ ፈተና |
| የፈጠራ ክሂሎት | **ምዕራፍ** 2:<br>2. የፈጠራ ክሂሎት (ክፍለ ጊዜ 28)<br>2.1. የሙዚቃ ኖታን መሰየምና መጻፍና ማንበብ (ክፍለ ጊዜ 10)<br>2.2. የበሎክ ህትመትና | ☞ የመስመሮችን ስያሜና ባዶ የሙዚቃ ሠንጠረዥ መሳልና መግለጽ፤ ክሌፎችን ከመነሻ ቦታቸዉ ጋር አለያይተዉ ማስተማር<br>☞ ሀሳብ፣ ስሜትንና በወቅቱ ያለዉን ሁኔታ በአጫጭር ቲአተርና ቪዲዮ በመግለጽ | ▪ የክፍል ዉስጥ ልምምድ<br>▪ የተቀረጸ ድምጽ፣ ቪዲዮ፣ ስዕሎች፣ ክለፎችና በሰሌዳ ላይ የተጻፉ ኖታዎች<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ የተለያዩ ጋዜጣና መጽሄቶች፣ ሙጫ፣ | • ምልከታ<br>• የግል ገለፃ<br>• የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የወረቀት ሞዛይክ ስራ (ክፍለ ጊዜ 9)<br>2.3. ባህላዊ አልባሳትንና መሳሪያዎችን በመጠቀም ትያትር ማሳየት /costume/props(ክፍለ ጊዜ 9) | ማስተማር<br>☞ ሞዛክን በወረቀትን በብሎክ ህትመት ሰርቶ ማሳየት<br>☞ (ስኳር ድንች፣ ካሮት፤ ቀይ ስርና የመሳሰሉት…) | እርሳስ፣ ክራወንና፣ በአከባቢያቸዉ የሚገኙ መሳሪያዎች<br>▪ ልብስና ለቲአተር የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች | |
| ባህላዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች | **ምዕራፍ** 3:<br>3. የስነጠበባት አጠቃላይ ባህላዊና ታሪካዊ ገፅታ (ክፍለ ጊዜ 20)<br>3.1. ህብራተሰቡ የሚጠ ቀምባቸዉ የባህላዊ ሙዚቃና ዉዝዋዜ አይነቶች (ክፍለ ጊዜ 7)<br>3.2. ታሪካዊ የስነጥበባት አይነቶች (የዋሻና ጥበባትና ቀለም ቅብ) (ክፍለ ጊዜ 6)<br>3.3. ስነቃል መንገር (ክፍለ ጊዜ ) | ☞ ህብራተሰቡ ውስጥ የሚገኙ የስነጥበብ ሰራዎችን በዜማ፣ ዉዝዋዘና ቲአተር ማስተማር<br>☞ በአከባቢዉ የሚታወቁ ባህላዊ ሙዚቃና ዉዝዋዜ ለይቶ ማስተማር<br>☞ በትዕይንትና በምልከታ ማስተማር | ▪ መለማመጃ ክፍል<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎች | • ምልከታ<br>• የግል ገለፃ<br>• የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ<br>• የቃል ጥያቄ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የስነጥበባት ሳቢነት | **ምዕራፍ** 4:<br>4. ስነጥበባትን ማስታወቅ (ክፍለ ጊዜ 22)<br>4.1. በስነጥበባት የሚገላጽ የሀሳብ ተመሳሳይነትና ልዩነት (ክፍለ ጊዜ 22) | ☞ ዝማሬ<br>☞ ዉዝዋዜ<br>☞ ቲአተር፣ ስዕልና ቪዲዮ<br>☞ የሀሳብ ተመሳሳይነትና ልዩነትን ስነጥበብን በመጠቀም በተግባር እያሳዩ ማስተማር<br>☞ ስነጥበብነ የእጅጥበብ በማህበረሰቡ ዉስጥ ያለዉ ጥቅም በማስመሰልና በማሳየት ማስተማር | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎች<br>▪ በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የምት ሙዚቃና የሌሎች መሳሪያዎች<br>▪ ስዕሎች፣ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎች<br>▪ ጥቃቅን የእጅ ጥበባትና ስዕሎች | • ምልከታ<br>• የግል ገለፃ<br>• የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ<br>• የቃል ጥያቄ<br>• የቤት ሥራ<br>• ፈተና |
| ትስስር፣ ግንኙነትና ተግባራዊነት | **ምዕራፍ** 5:<br>5. የስነጥበባት ትስስር ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር (ክፍለ ጊዜ 23)<br>1.1.1 ዝማሬ፣ ዉዝዋዜና ቲአተርን በተጠቀም የትራፊክ አደጋን፣ የኤችአይቪ በሽታን፣ አደንዛዥ ዕጾችን, (ወቅጣዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ) እና የመሳሰሉትን ያሳያሉ) (ክፍለ ጊዜ 13)<br>1.2 በማህበረሰቡ ዉስጥ ያሉ ምልክቶች (ማስታወቂያና አርማ) (ክፍለ ጊዜ 10) | ☞ በቡድን ማዜም፣ መወዛወዝ፣ ትአተርን ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናኘት ማስተማር<br>☞ በማህበረሰቡ ዉስጥ ያሳ ምልክቶችንና ወካዮችን ይረዳሉ | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ<br>▪ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎች<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻ<br>▪ በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የምት ሙዚቃና የሌሎች መሳሪያዎች፣ የመድረክ ጨዋታዎች...<br>▪ ስዕሎች፣ የድምጽና የቪዲዮ መቅረጫ መሣሪያዎች<br>▪ ሎጎ፣ ፖስተርና በአከባቢ የሚገኙ መሰሪያዎች | • ምልከታ<br>• የግል ገለፃ<br>• የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ<br>• የቃል ጥያቄ<br>• የቤት ሥራ<br>• ፈተና |